(1)

ግብጽ አረብ ሪፐበሊክ ረቢዕ ሳኒ 7/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር ኑቬምበር 12/2021 ግ.

# የመከራና የመፍትሄ ሁኔታዎች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

"وَإِذْ تَأَذَّنَ رَبُّكُمْ لَئِنْ شَكَرْتُمْ لَأَزِيدَنَّكُمْ"

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም

(ጌታችሁም «ብታመሰግኑ በእርግጥ እጨምርላችኋለሁ፡፡... በማለት ባስታወቀ ጊዜ) አስታውስ፡፡ ማለት ነው፡፡

ብቸኛ አጋር የሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ እንድሁም ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸው እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) በምድር ካሰቀመጣቸው ደንቦች መካከል አንዱ ሕይወትን ከመከራና መፍትሄ፣ ከጭንቅና ተድላ እንዲሁም ከሐዘንና ደስታ አዙሪኝ ውስጥ እንትሽከረከር ማድረጉ ነው፡፡ የአምነት ባለቤቶችም

እነዚያ በሁሉም በተጠቀሱት ሁኔታዎች ከትግስትና ምስጋና መስመር የማወጡት ናቸው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (የሙእሚን ነገር የሚገርም ነው፡፡ በእርግጥ የሱ ነገሩ ሁሉ ደግ ነገር ነው፡፡ ያም ለሙእሚን እንጂ ለሌላ ለማንም አይሆንም፡፡ ደስታዎች ቢያጋጥሙት ያመሰግናል፡፡ መከራዎች ቢደርሱበትም ይታገሳል፡፡ ይህም ለሱ መልካም ነገር ይሆንለታል፡፡)

ከአላህ (ሱ.ወ.) ውብ *ሥራዎች* መካከል አንዱ ከጭንቅ በኋላ መፍተሄ ከችግርም በኋላ ምችቾት እንዲመጣ ማድረጉ ነው፡፡ እሱም (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

**{فَإِنَّ مَعَ العُسْرِ يُسْرًا * إِنَّ مَعَ العُسْرِ يُسْرًا}**

(ከችግርም ጋር ምቾት አልለ፡፡ ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾት አልለ፡፡)

አላህ በአስቀመጠው ደንብ መሰረት አንድ ነገር ከጠበበ በኋላ ይሰፋል፡፡ አንድ ችግርም ሁለት ምቾቶችን ሊያሸንፍ አይችልም፡፡ ከጭንቅ በኋላ መፍትሄ፣ ከችግር በኋላም መቾት የማይቀር ነገር ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ (መፍትሄ ከጭንቅ በኋላ ነው፡፡ ከችግር ጋርም ምቾት አለ፡፡)

የነብያትን የሕይወት ታሪክ የሚመራመር ሰው የዚህን ጉዳይ ትርጉም በግልጽ ሊገነዘበው ይችላል፡፡ እነሆ ነብዩ ያዕቆብ (ዐ.ሰ.) ከልጆቻቸው መካከል በጣም የሚወዱትን ነብዩ ዩሱፍን (ዐ.ወ.) ያጣሉ፡፡ ከዓመታት በኋላም ሁለተኛ ልጃቸውን ያጣሉ፡፡ በሁለቱ ልጆቻቸው መለየት ምክንያት ልቅሱዋቸውና ሐዘናቸው በዝቶ ዓይናቸውን ያጣሉ፡፡

**"وَابْيَضَّتْ عَيْنَاهُ مِنَ الْحُزْنِ فَهُوَ كَظِيمٌ"**

ዓይኖቹም ከሐዘን (ለቅሶ) የተነሳ ነጡ፡፡ እርሱም በትካዜ የተሞላ ሆነ፡፡)

ሆኖም ምንም ተስፋ አልቆረጡም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) በቅዱስ ቁርኣን ታሪኩን እንዲህ በማለት አውስቶታል፡፡

**"يا بَنِيَّ اذْهَبُوا فَتَحَسَّسُوا مِنْ يُوسُفَ وَأَخِيهِ وَلا تَيْأَسُوا مِنْ رَوْحِ اللَّهِ إِنَّهُ لا يَيْأَسُ مِنْ رَوْحِ اللَّهِ إِلاَّ الْقَوْمُ الْكَافِرُونَ"**

(«ልጆቼ ሆይ! ሂዱ፤ ከዩሱፍና ከወንድሙም (ወሬ) ተመራመሩ:: ከአላህም እዝነት ተስፋ አትቁረጡ:: እነሆ ከአላህ እዝነት ከሓዲዎች ሕዝቦች እንጂ ተስፋ አይቆርጥም» (አለ)::

ከዚያም ከባድ ችግርና መከራ በኋላ ከአላህ ዘንድ መፍትሄው ይመጣላቸዋል:: አላህም ዓይኖቻቸውንና ሁለት ልጆቻቸውንም ይመልስላቸዋል:: እሱም(ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡

**"فَلَمَّا أَنْ جَاءَ الْبَشِيرُ أَلْقَاهُ عَلَى وَجْهِهِ فَارْتَدَّ بَصِيرًا قَالَ أَلَمْ أَقُلْ لَكُمْ إِنِّي أَعْلَمُ مِنَ اللَّهِ مَا لا تَعْلَمُونَ".**

(አብሳሪውም በመጣ ጊዜ (ቀሚሱን) በፊቱ ላይ ጣለው:: ወዲውም የሚያይ ኾነ:: «እኔ ለእናንተ፡- ከአላህ በኩል የማታውቁትን ዐውቃለሁ አላልኳችሁምን» አላቸው::)

አላህ (ሱ.ወ.) ነብዩ ዩኑስን (ዐ.ሰ.) ከባሕር፣ ከሌሊትና ከአሳ ነባሪ ሆድ ጨለማዎች በማዳኑ ችግሩ ወደእልባት፣ መከራው ወደመፍትሄ ተለውጧል:: ታላቁ አላህ እንዲህ ይላል፡

**"وَذَا النُّونِ إِذْ ذَهَبَ مُغَاضِبًا فَظَنَّ أَنْ لَنْ نَقْدِرَ عَلَيْهِ فَنَادَى فِي الظُّلُمَاتِ أَنْ لا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ سُبْحَانَكَ إِنِّي كُنْتُ مِنَ الظَّالِمِينَ* فَاسْتَجَبْنَا لَهُ وَنَجَّيْنَاهُ مِنَ الْغَمِّ وَكَذَلِكَ نُنْجِي الْمُؤْمِنِينَ".**

(የዓሳውንም ባለቤት ተቆጥቶ በኼደ ጊዜ (አስታውስ):: በእርሱም ላይ ፈጽሞ የማንፈርድበት መኾናችንን ጠረጠረ:: (ዓሳም ዋጠው):: በጨለማዎችም ውስጥ ኾኖ ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም:: ጥራት ይገባህ:: እኔ በእርግጥ ከበዳዮቹ ነበርኩ በማለት ተጣራ::)

አላህ (ሱ.ወ.) ለነብዩ ዘከሪያ (ዐ.ሰ.) እድሚያቸው ከገፋ፣ አጥንታቸው ከሳሳ፣ ስጋቸው ከተዳከመና ራሳቸውም ከሸበተ በኋላ ጸሎታቸውን በመቀበል ልጅን ስጥቷቸዋል፡፡ ይህንም አላህ እንዲህ በማለት ገልጾታል፡

**"قَالَ رَبِّ هَبْ لِي مِنْ لَدُنْكَ ذُرِّيَّةً طَيِّبَةً إِنَّكَ سَمِيعُ الدُّعَاءِ * فَنَادَتْهُ الْمَلَائِكَةُ وَهُوَ قَائِمٌ يُصَلِّي فِي الْمِحْرَابِ أَنَّ اللَّهَ يُبَشِّرُكَ بِيَحْيَى مُصَدِّقًا بِكَلِمَةٍ مِنَ اللَّهِ وَسَيِّدًا وَحَصُورًا وَنَبِيًّا مِنَ الصَّالِحِينَ".**

(«ጌታዬ ሆይ! ከአንተ ዘንድ መልካም ዘርን ለኔ ስጠኝ አንተ ጸሎትን ሰሚነህና» አለ፡፡ እርሱም በጸሎት ማድረሻው ክፍል ቆሞ ሲጸልይ መላእክት ጠራችው፡፡ «አላህ በየሕያ ከአላህ በኾነ ቃል የሚያረጋግጥ ጌታም ድንግልም ከደጋጎቹ ነቢይም ሲኾን ያበስርሃል» በማለት (መላእክት ጠራችው)፡፡

የእስልምና ሃይማኖት ህግጋቶችን የሚመራመር ሰው አላህ (ዐ.ወ.) ለጭንቅ መፍትሄ በርካታ በሮችንና መክፈቻዎችን ያደረገ መሆኑን ይገነዘባል፡፡ ከነሱም መካከል በቅድሚያ የሚጠቀሱት፡ ፈሩሃ አላህነትን አጥብቆ መያዝ፣ በጸሎት ወደ አላህ (ሱ.ወ.) መጠጋትና አላህን ማውሳት የሚሉት ናቸው፡፡ ታላቁ አላህ እንድህ ይላል፡

**"وَمَنْ يَتَّقِ اللَّهَ يَجْعَلْ لَهُ مَخْرَجًا * وَيَرْزُقْهُ مِنْ حَيْثُ لَا يَحْتَسِبُ وَمَنْ يَتَوَكَّلْ عَلَى اللَّهِ فَهُوَ حَسْبُهُ إِنَّ اللَّهَ بَالِغُ أَمْرِهِ قَدْ جَعَلَ اللَّهُ لِكُلِّ شَيْءٍ قَدْرًا"**

(አላህንም የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል፡፡ ከማያስበውም በኩል ሲሳየን ይሰጠዋል፡፡ በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው፡፡ አላህ ፈቃዱን አድራሽ ነው፡፡ አላህ ለነገሩ ሁሉ የተወሰነ ጊዜን በእርግጥ አድርጓል፡፡) እንዲሁም እንድህ ይላል፡

**"أَمَّن يُجِيبُ الْمُضْطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكْشِفُ السُّوءَ وَيَجْعَلُكُمْ خُلَفَاءَ الْأَرْضِ أَإِلَٰهٌ مَّعَ اللَّهِ قَلِيلًا مَّا تَذَكَّرُونَ"**

(ወይም ያ ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል፣ መከራንም የሚያስወግድ፣ በምድርም ላይ ምትኮች የሚያደረጋችሁ፤ (ይበልጣልን ወይስ የሚያጋሩት) ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን ጥቂትንም አትገሠጹም፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጭንቀት በሚያጋጥማቸው ጊዜ በሚከተሉት ቃለት ይጸልዩ እንደነበር ባልደረቦቻቸው ዘግበዋል፡

**(لا إلهَ إلا اللهُ العظيمُ الحليمُ، لا إلهَ إلا اللهُ ربُّ العرش العظيم، لا إلهَ إلا اللهُ ربُّ السماواتِ وربُّ الأرض رب العرش الكريم)**

እንዲህም ይላሉ፡ (ሀሳብ፣ ወይም ጭንቀት፣ ወይም ህመም፣ ወይም ችግር ያጋጠመው ሰው

**اللهُ ربِّي لا شريكَ لهُ**

ካለ እነዚህ ችግሮች ይወገዱለታል፡፡)

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

አንድ ሰው በችግርም ሆነ ችግር በሌለበት፣ በበሽታም ሆነ በጤንነት ወቅት ዘወትር አላህን የሚያሳ መሆኑ ምንኛን ያስደስታል፡፡ ማንኛውም

ሰው ከሚሰሩት ስራ አላህ ከአስጠነነቀቀን በጤንነትና ችግር በማይኖርባቸው ጊዜ አላህን ከሚረሱና ለችሮታውም ምስጋናን ከማያደርሱ ወገሞች እንዳይካተት ሊጠነቀቅ ይገባል፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

"وَإِذَا مَسَّ الإِنْسَانَ ضُرٌّ دَعَا رَبَّهُ مُنِيبًا إِلَيْهِ ثُمَّ إِذَا خَوَّلَهُ نِعْمَةً مِنْهُ نَسِيَ مَا كَانَ يَدْعُو إِلَيْهِ مِنْ قَبْلُ وَجَعَلَ لِلَّهِ أَنْدَادًا لِيُضِلَّ عَنْ سَبِيلِهِ"

(ሰውንም ጉዳት ባገኘው ጊዜ ጌታውን ወደርሱ ተመላሽ ኾኖ ይጠራል፡፡ ከዚያም ከእርሱ ዘንድ ጸጋን በሰጠው ጊዜ ያንን ከዚያ በፊት ወደርሱ ይጸልይበት የነበረውን (መከራ) ይረሳል፡፡ ከመንገዱ ለማሳሳትም ለአላህ ባላንጣዎችን ያደርጋል፡፡)

እንዲሁም እንድህ ይላል፡

"وَإِذَا مَسَّ النَّاسَ ضُرٌّ دَعَوْا رَبَّهُمْ مُنِيبِينَ إِلَيْهِ ثُمَّ إِذَا أَذَاقَهُمْ مِنْهُ رَحْمَةً إِذَا فَرِيقٌ مِنْهُمْ بِرَبِّهِمْ يُشْرِكُونَ"

(ሰዎችንም ችግር ባገኛቸው ጊዜ ጌታቸውን ወደርሱ ተመላሾች ሆነው ይጠሩታል፡፡ ከዚያም ከእርሱ ችሮታን ባቀመሳቸው ጊዜ ከእነርሱ ከፊሎቹ ወዲያውኑ በጌታቸው (ጣዖትን) ያጋራሉ፡፡)

እንዲሁም እንድህ ይላል፡

"وَإِذَا مَسَّكُمُ الضُّرُّ فِي الْبَحْرِ ضَلَّ مَنْ تَدْعُونَ إِلَّا إِيَّاهُ فَلَمَّا نَجَّاكُمْ إِلَى الْبَرِّ أَعْرَضْتُمْ وَكَانَ الإِنْسَانُ كَفُورًا"

(በባሕሩም ውስጥ ጉዳት ባገኛችሁ ጊዜ የምትጠሩዋቸው (አማልክት) ሁሉ ከእርሱ (ከአላህ) በቀር ይጠፋሉ፡፡ ወደ የብስም በማድረስ ባዳናችሁ ጊዜ (እምነትን) ትተዋላችሁ፡፡ ሰውም በጣም ከሓዲ ነው፡፡)

አሁንም እንድህ ይላል፡

"وَإِذَا مَسَّ الإِنْسَانَ الضُّرُّ دَعَانَا لِجَنْبِهِ أَوْ قَاعِدًا أَوْ قَائِمًا فَلَمَّا كَشَفْنَا عَنْهُ ضُرَّهُ مَرَّ كَأَنْ لَمْ يَدْعُنَا إِلَى ضُرٍّ مَسَّهُ كَذَلِكَ زُيِّنَ لِلْمُسْرِفِينَ مَا كَانُوا يَعْمَلُونَ"

(ሰውንም ጉዳት ባገኘው ጊዜ በጎኑ ላይ ተጋድሞ ወይም ተቀምጦ ወይም ቆሞ ይለምነናል፡፡ ጉዳቱንም ከእሱ ላይ በገለጥንለት ጊዜ ወደ አገኘው ጉዳት እንዳልጠራን ሆኖ ያልፋል፡፡ እንደዚሁ ለድንበር አላፊዎች ይሠሩት የነበሩት ሥራ ተሸለመላቸው፡፡)

እንድህም ይላል፡

**"قُلْ مَن يُنَجِّيكُم مِّن ظُلُمَاتِ الْبَرِّ وَالْبَحْرِ تَدْعُونَهُ تَضَرُّعًا وَخُفْيَةً لَّئِنْ أَنجَانَا مِنْ هَٰذِهِ لَنَكُونَنَّ مِنَ الشَّاكِرِينَ"**

(ከየብስና ከባሕር ጨለማዎች በግልጽና በምስጢር የምትጠሩት ስትኾኑ «ከነዚህ ቢያድነን በእርግጥ ከአመስጋኞች እንኾናለን (ስትሉ) የሚያድናችሁ ማነው» በላቸው፡፡)

እነዚህ አንቀጾች የነዚያን በመከራና በችግር ጊዜ በጸሎት ወደአላህ የሚዋደቁትን ከነሱም ጉዳትን ባስወገደላቸውና መከራንም ባነሳለቸው ጊዜ ከዚያ በፊት ወደነበሩበት አስከፊ ሁኔታ የሚመለሱትን ሰዎች ገጽታ ይቀርፃሉ፡፡

እኛ በአሁኑ ወቅት በድሎት ጊዜ የአላህን ችሮታ ማመስገን በመከራና በችግር ወቅትም በትእግስት መታነጽ እጅጉን ያስፈልገናል፡፡ እንዲሁም በድሎትም ሆነ በችግር ጊዜ ዘወትር አላህን ማስታወስ ይገባናል፡፡ ነብያችን (ሱ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በመከራና በጭንቅ ጊዜ የሚያደረገውን ጸሎት አላህ እንዲቀበለው የሚፈልግ ሰው በድሎት ጊዜ ጸሎትን ያብዛ)፡፡ እንዲሁም እንድህ ይላሉ፡ (በድሎት ጊዜ አላህን አስታውስ በመከራ ጊዜ ጸሎትህን ይቀበልልሃልና፡፡

አቡ ደርዳእ የተባሉት የነብያችን ባልደረባ እንዲህ ይላሉ፡ ‹‹በድሎትህ ቀን አላህን ለምን በችግርህ ቀን አላህ ጸሎትህን ይቀበልሃል፡፡››

ጌታችን ሆይ! የተጨነቁን ሁሉ ጭንቀት አስወግድ፡፡ ተድለና ችሮታህን እንዲናመሰግን እገዛህ ከኛ ጋር ይሁን፡፡ አሚን፡፡